የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 1 እና 2

1. ከአራቱ ወቅቶች ቅዱስ ዮሐንስ በየትኛው ይመሰላል? ምክንያቱስ ምንድን ነው?
ሀ) ጸደይ፤ የዘርን ምሳሌ ከሁሉ አምልቶ ስለጻፈ.
ለ) መጸው፤ በነፋስ አምሳል መንፈስ ቅዱስ እንደሚሰጥ ተናግሯልና
ሐ) በጋ፤ መስተጻርርና መስተቃርን የሌለበት ደረቅ ቃል በመጀመሪያ ቃል ነበር... እያለ ጽፏልና
መ) ክረምት፤ ወንጌሉን በጌታችን ጥምቀት ይጀምራልና

2. ከሚከተሉት ውስጥ የቅዱስ ዮሐንስ ስም ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ) ቦኣኔርጌስ ለ) አቡቀለምሲስ ሐ) ታዖነሎስ መ) ፍቁረ እግዚእ ሠ) መልሱ አልተሰጠም

3. ዮሐንስ ወንጌላዊ ጌታችንን ከመከተሉ በፊት የማን ደቀመዝሙር ነበር?
ሀ) የፊሪሳውያን ለ) የገማልያል ሐ) የመጥምቁ ዮሐንስ መ) የማንም ተከታይ አልነበረም

4. የዮሐንስ ወንጌል ስንት ምዕራፍ አለው?
ሀ)28 ለ)24 ሐ)21 መ)16

5. የዮሐንስ ወንጌልን የፃፈው ማን ነው?
ሀ)መጥመቁ ዮሐንስ ለ)ዮሐንስ ወልደዘብዴዎስ ሐ)ዮሐንስ አፈወርቅ መ)ሁሉም

6. ቅዱስ ዮሐንስ በንስር የተመሰለው ለምንድን ነው?
ሀ) ንስር በእግሩ እንዲሽከረከር ዮሐንስም ወልደ ዕጓለ እመሕያው ከሰማይ መውረዱን ይጽፋልና
ለ) ንስር በክንፉ መጥቆ እንዲበር ዮሐንስም አካል ከህልውና ተገልጾለት ቀዳሚሁ ቃል ብሎ ተናግሯልና
ሐ) የንስር ዓይኑ ጽሩይ እንደሆነ ሁሉ ዮሐንስ ንጽሐ ሥጋና ነፍስ ተሰጥቶት ረቂቅ የሆነውን ምሥጢር አጉልቶ አይቶ ቀዳሚሁ ቃል ብሎ ተናግሯልና
መ) ሁሉም መልስ ናቸው

7. የዮሐንስ ወንጌልን የጻፈው ሰው የሚቆጠረው ከነማን ጋር ነው?
ሀ)ከ12ቱ ሐዋርያት ለ)ከ318ቱ ሊቃውንት ሐ)ከ72ቱ አርድእት መ)ሁሉም

8. ስለ ቅዱስ ዮሐንስ የማስተማር ሕይወት ትክክል የሆነው የቱ ነው?
ሀ) ሐዋርያት ለስብከተ ወንጌል በዕጣ ሲከፋፈሉ ምድረ ግሪክ(ጽርዕ) ደርሳዋለች
ለ) ሊያስተምር የተላከው ወደኤፌሶን ሲሆን በዚያ አርጤምስ የምትባል ሴት ትመለክ ነበር
ሐ) ዮሐንስ ወደ ጽርዕ ኤፌሶን የሄደው ከደቀመዝሙሩ ከአብሮኮሮስ ጋር ነው
መ) ሁሉም መልስ ናቸው

9. የዮሐንስ ወንጌል ከሌሎቹ ወንጌሎች የሚለየው በምንድን ነው?
ሀ) ሌሎቹ በታሪኮች ላይና ጌታችን ባደረጋቸው ተአምራት ላይ ያተኮሩ ሲሆን እርሱ ግን የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት በመግለጥ ላይ ያተኩራል
ለ) እንደ ቅዱስ ሉቃስ በጽንሰቱ ሳይሆን እንደ ቅዱስ ማቴዎስ በሐረገ ትውልዱ ጀምሮ ይጽፋል
ሐ) ዮሐንስ የመዘገባቸው አብዛኞቹ ቃላት የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት አጉልተው የሚያሳዩ ናቸው
መ) ሀ እና ሐ

10.በዮሐንስ ወንጌል ቃል ተብሎ የተገለፀው ማን ነው?
ሀ)እራሱ ጸሐፊው ለ)መጥመቁ ዮሐንስ ሐ)ናትናኤል መ)ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ

11. ቃል_____
ሀ)እግዚአብሔር ነው ለ)በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ሐ)ስጋ ሆነ መ)ሁሉም

12.የዮሐንስ ወንጌል በአጀማመሩ ከየትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ ጋር ያመሳስለዋል?
ሀ)ኦሪት ዘፍጥረት ለ)የማቴዎስ ወንጌል ሐ)የሉቃስ ወንጌል መ)የማርቆስ ወንጌል

13.ስለ ቃል እውነት ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ) አተር.ጋዎን የመላእክት ቃል ነው
ለ) ቦርፎሪኮን ነቢያት ከእግዚአብሔር ዘንድ የሰሙት ቃል ነው
ሐ) አአትሪኮን በአየር የሚፈሰው ቃላችን/የሰው ቃል/ ነው
መ) መልሱ አልተሰጠም

14.መጥመቁ ዮሐንስ ስለጌታችን ከመሰከረው ውስጥ ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ)የዓለሙን ኀጢኣት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ
ለ)የጫማውን ጠፍር ልፈታ የማይገባኝ ነው
ሐ)እርሱ በውኃ፣ እኔ በመንፈስ ቅዱስ ነው የማጠምቀው
መ)መልስ አልተሰጠም

15.የመጥመቁ ዮሐንስ ደቀመዝሙር እንደነበረ በግልፅ የተነገረው ስለማን ነው?
ሀ)ፊልጶስ ለ)እንድርያስ ሐ)ኢሳይያስ መ)ሙሴ

16.ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለናትናኤል የነገረው ሐዋርያ ማን ነው?
ሀ)ኬፋ ለ)ጳውሎስ ሐ)ፊልጶስ መ)እንድርያስ

17.ጌታችን ናትናኤልን ከበለስ በታች ሳለህ አየሁህ ያለው መቼ ነው?
ሀ)በሕፃንነቱ ከሄሮድስ ጭፍሮች ለማስመለጥ እናቱ በቀፎ አድርጋ ስትደብቀው

ለ)ሰው ገድሎ ሲያስቀብር
ሐ)ባለጸጋ ስለነበር ወያፋፍን ሲያስፈትን እና ፊረስ እና በቅሎ ሲያስገራ ይውል ነበር
መ)ሁሉም

18.በመጽሐፍ ቅዱስ ባህል "ካንቺ ጋር ምን አለኝ " የሚለው አነጋገር የምን መግለጫ ነው?
ሀ)የጥላቻ
ለ)የክርክር
ሐ)በመካከል ምንም ጠብ እና ቅራኔ እንደሌለ ማሳያ
መ)ሁሉም

19.ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ውኃን ወደ ወይን የቀየረው በየት ነው?
ሀ)በቃና ዘገሊላ ለ)በቤተመቅደስ ሐ)በግብፅ መ)ለ እና ሐ

20. እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወይኑ ማለቁን ማን ነገራት?
ሀ)የወይን አሳላፊው ለ)ከሐዋርያት አንዱ ሐ)ሙሽራው መ)ማንም አልነገራትም

21.ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰርግ ቤት ያደረገው ውኃን ወደ ወይን የቀየረው እንዴት ነው?
ሀ)ቀጥታ ውኃን ወደ ወይን በመለወጥ
ለ)ትንሽ የነበረውን ወይን በማበርከት
ሐ)ወይን እና ውኃን በመቀላቀል
መ)ሁሉም

22. በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 2 ላይ የቤትህ ቅናት በላኝ የሚለውን ቃል ያሰቡት እነማን ናቸው?
ሀ)ሐዋርያት ለ)ፈሪሳውያን ሐ)ነቢያት መ)ሳምራውያን

23. የአይሁድ ቤተመቅደስ ለመሠራት ስንት ጊዜ ፈጀ?
ሀ)46 ቀን ለ)3 ቀን ሐ)3 ዓመት መ)46 ዓመት

24. "ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፥ በሦስት ቀንም አነሣዋለሁ" ሲል ጌታችን ስለምን እየተናገረ ነበር?
ሀ)ስለሰውነቱ ለ)ስለአይሁድ ቤተመቅደስ ሐ)ስለኢየሩሳሌም መ)ሀ እና ለ

25. በምዕራፍ 2 ከቁጥር 4 ላይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እናቱን “አንቺ ሆይ ካንቺ ጋር ምን አለኝ? ጊዜዬ ገና አልደረሰም” ያላት ምን ለማለት ፈልጎ ነው?
ሀ) ውኃውን የወይን ጠጅ አድርግላቸው ብትዪኝ አይሆንም እልሽ ዘንድ ካንቺ ጋር ምን ፀብ አለኝ?
ለ) መጽሐፍ እግዚአብሔር ሥራውን የሚሠራበት ጊዜ አለው እንዲል ሥራዬን የምገልጥበት ጊዜዬ አልደረሰም ሲል ነው
ሐ) በአምላክነቱ አጉበሮ ተአዝዞ እንደሌለበት ለማጠየቅ ነው
መ) ለሕይወታቸው መዳኛ የሚሆናቸውን ወይን(ደሜን) አፍስሼ ለሰው ልጆች እሰጣቸው ዘንድ የምሰቀልበት ጊዜ ገና አልደረሰም
ሠ) ሁሉም